ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን የመለየት እና የማስተማር ሂደትን መረዳት 2026–2027

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ IOA-RA፣ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ትምህርት፣ እና የሜሪላንድ ኮድ ደንብ 13A.04.07፣ ባለ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ትምህርት የተማሪዎችን ተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) ሁለንተናዊ የማጣሪያ ሂደት ላይ ይሳተፋሉ። ("የተፋጠነ ትምህርት" ማለት በተማሪው(ዋ) ትምህርት የመቀበል አቅም ላይ በመመርኮዝ ከመደበኛው የክፍል ደረጃ ቀደም ብሎ ኮርስ መውሰድ ማለት ሲሆን "ከፍተኛ/የዳበረ ትምህርት" ማለት ደግሞ አንድን ትምህርት ወይም ኮርስ በከፍተኛ ጥልቀት ይማሩታል ማለት ነው።) የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) 2ኛ ክፍል ተማሪዎች በሙሉ ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) ሁለንተናዊ የማጣራት ሂደት ላይ ይሳተፋሉ። በተጨማሪም፣ በአሁኑ ወቅት 4ኛ እና 7ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች፣ ወደ MCPS አዲስ የመጡ እና ከዚህ ቀደም «ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች» (gifted and talented) መስፈርት ያላሟሉ ተማሪዎች፣ በዚህ የትምህርት አመት ለዚህ ምድብ ብቁ መሆናቸው ይጣራል። GT (ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን) የመለየት ሂደት፣ ተማሪዎች ያላቸውን ጠንካራ ጎኖች በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህ መረጃ ተማሪዎችን ለይቶ ለማወቅ እና ለቀጣዩ የትምህርት አመት የማስተማር እቅድ ለማዘጋጀት ያገለግላል። በሜይ ወር፣ ወላጆች የተማሪዎቻቸውን «ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው» (gifted and talented) ተብለው መለየታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል። ተማሪዎች በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት የበለጸገ እና/ወይም የተፋጠነ ትምህርት እድሎችን ለማግኘት በይፋ ባለተሰጥኦ እና ምጡቅ ችሎታ ልየታ አያስፈልጋቸውም።

ልዩ ተሰጥኦ እና የትምሕርት ብቃት ያላቸውን ተማሪዎች የመለየት ሂደት፣ MCPS የአንደኛ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ‘በማዕከላዊ ደረጃ ከሚደረገው ግምገማ’ (Central Review) እንዲሁም ወደ ‘ማግኔት’ (magnet) ትምህርት ቤቶች የመግቢያ ሂደት ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው። የባለ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ (GT) ስያሜ በአንደኛ ደረጃ የበለጸገ ትምህርት ጥናት ወይም የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማግኔት ትምህርት (ሰብአዊነት እና ኮሙኒኬሽን፤ ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ኮምፒውተር ሳይንስ) የማጣራት ሒደት አይደለም። በአካባቢ ትምህርት ቤት የበለፀገ እና የተፋጠነ የትምህርት ምደባ ለማግኘት GT ስያሜ የላቀ አካዴሚያዊ ክንዋኔዎች እና/ወይም እምቅ አቅምን ከሌሎች መረጃዎች ጋር የማቀናጀት ተግባር ጋር ነው። ትምህርት ቤቶች በመሠረታዊ የትምህርት ይዘት መስኮች ትምህርት ማበልፀግ እና ማፋጠንን በተመለከተ የተማሪዎችን መረጃ ይከታተላሉ እና ይመረምራሉ።

2026–2027 ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው ጎበዝ ተማሪዎችን የመለየት ሂደት ላይ ምን አይነት የመረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ይውላሉ?

GT (ልዩ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ) ለይቶ ማወቅ ሂደቱ፣ የግንዛቤ ብቃት ምዘናን፣ የአካዳሚክ ምዘናዎችን፣ እና የባህሪ መገለጫ ዝርዝሮችን ጭምር በርካታ የመረጃ ምንጮችን ይጠቀማል። የጸደይ/ስፕሪንግ ወቅት 3ኛ ክፍል የሜሪላንድ አጠቃላይ የግምገማ ፕሮግራም (MCAP) ውጤቶች ለአሁኑ 4ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ እንዲሁም 6ኛ ክፍል የጸደይ/ስፕሪንግ ወቅት ውጤቶች ለአሁኑ 7ኛ ክፍል ተማሪዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

2ኛ፣ 4ኛ፣ እና 7ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በመላው የትምሕርት ስርዓቱ ለሚካሄደው ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ (GT) የመለየት ስራ፣ የሚከተሉትን የመረጃ ምንጮች ይጠቀማል፦

የግንዛቤ ግምገማ፦

- **የግንዛቤ ችሎታ ምዘና/Cognitive Abilities Test (CogAT)Full Battery: 2ኛ እና 4ኛ ክፍል መደበኛ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ለመለየት ተግባራዊ የሚደረጉ የአዕምሮ ብቃት ምዘናዎች (CogAT ወይም Cognitive Abilities Test) የመሣሰሉ ፈተናዎች ስብስብ፡ በስዕሎች፣ በቅርጻቅርጾች ወይም በቃል በሚቀርቡ ጥያቄዎች አማካኝነት፣ ወጣት ተማሪዎች ያላቸውን የማመዛዘን እና ችግር የመፍታት ችሎታ መገምገም።**

የትምህርት ምዘናዎች፡-

- **መሠረታዊ ቀደምት የሊተርሲ ችሎታ እድገት አመልካቾች** (DIBELS): **2ኛ ክፍል**
- Lectura (**ስፓንሽኛ ትርጉም** DIBELS): **2ኛ ክፍል ስፓንሽኛ ኢመርሽን**
- **የአካዳሚክ እድገት ምዘና** (MAP) - **ንባብ፡ 4ኛ እና 7ኛ ክፍል**
- **የአካዳሚክ እድገት መለኪያዎች** (MAP) - **ሂሳብ፡ 2ኛ፣ 4ኛ፣ እና 7ኛ ክፍል**
- **የሜሪላንድ አጠቃላይ የትምህርት ግምገማ ፕሮግራም** (MCAP) **እንግሊዝኛ/የቋንቋ ስነጥበብ፡ 4ኛ እና 7ኛ ክፍል**
- **የሜሪላንድ አጠቃላይ የትምህርት የግምገማ ፕሮግራም** (MCAP) **ሂሳብ፡ 4ኛ እና 7ኛ ክፍል**

ዝርዝር የባህሪ ማረጋገጫ፡-

- **የወላጅ ግብአት ቅጽ(ቅጾች): 2ኛ፣ 4ኛ፣ እና 7ኛ ክፍል**
- **የክፍል መምህር ዳሰሳ፡ 2ኛ እና 4ኛ ክፍል**
- **እንግሊዝኛ/ንባብ እና ሂሳብ የመምህራን ዳሰሳ፡ 7ኛ ክፍል**
- **የሰራተኞች ድጋፍ መግለጫ ቅጽ (ካስፈለገ)፡- 2ኛ፣ 4ኛ፣ እና 7ኛ ክፍል**

2026-2027 የትምህርት አመት ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) ምደባ በተለይ የክፍል ደረጃ መስፈርት ለማየት ከዚህ በታች ያለውን የክፍሎችን ደረጃ ጠቅ ያድርጉ።

2ኛ ክፍል 4ኛ ክፍል 7ኛ ክፍል

2ኛ ክፍል የትምህርት አመት (SY) 2026-2027

2ኛ ክፍል ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች (GT) ለመለየት አራት መንገዶች አሉ። በዘንድሮው ዓመት የውጭ መረጃ ምንጮች ውስን በመሆናቸው፣ ከ 2025 የጸደይ ወቅት የመዋእለ ህጻናት (Kindergarten) እና ከ 2026 የጸደይ ወቅት የአንደኛ ክፍል ተማሪዎች መረጃዎችም ጥቅም ላይ ይውላሉ። ለእያንዳንዱ ዘርፍ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከዚህ በታች ተገልጸዋል። MAP ውጤቶች በአካባቢያዊ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚጠበቁ ናቸው።

የመረጃ ምንጮች	**ጠቋሚ**
የመጀመሪያው 1ኛው መንገድ፡ የግንዛቤ መለኪያ ብቻ መሟላት አለበት።	
የግንዛቤ መለኪያ፡-	
CogAT **(የፈተና/የግምገማ ጊዜ** 12/14/26-12/17/26)	**ከተፈታኞች ጥምር ውጤት** - 90 **ፐርሰንት ወይም ከዚያ በላይ**
2ኛው መንገድ፡ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) እና አንድ መፃፍ እና አንድ የሂሳብ መለኪያ መሟላት አለበት።	
የግንዛቤ መለኪያ፡-	
CogAT **(የፈተና/የግምገማ ጊዜ** 12/14/26-12/17/26)	85ኛ - 89ኛ **ጥምር ውጤት በመቶኛ** (Composite - 85th - 89th percentile)
የአካዳሚክ ውጤት ምዘና፡-	
መዋእለ ህጻናት ፀደይ/ስፕሪንግ 2025 DIBELS **(የፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት ግምገማ ወቅት** 04/05/25-06/12/25) **<u>ወይም</u>** **መዋዕለ ሕፃናት 2025 ፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት** Lectura **(ስፓንሽኛ ትርጉም)** **(የፀደይ/የስፕሪንግ ግምገማ ወቅት** 04/05/25-06/12/25)	**የፀደይ/የስፕሪንግ** 2025 DIBELS **የተቀናጀ ውጤት** 450 **ወይም ከዚያ በላይ** **<u>ወይም</u>** **ጸደይ/ስፕሪንግ** 2025 Lectura 438 **ወይም ከዚያ በላይ**
1ኛ ክፍል የትምሕርት አመት 2026 የጸደይ/የስፕሪንግ ወቅት ሂሳብ MAP Growth **(ፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት የግምገማ ወቅት** 12/04/26-06/05/26)	2026 ጸደይ/ስፕሪንግ ወቅት 85% ወይም ከዚያ በላይ

3ኛው መንገድ፣ የግንዛቤ መለኪያ እና አንድ የአካዳሚክ መለኪያ (ሊተርሲ ወይም ሂሳብ) እና አንድ የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር መሚላት አለበት።	
የግንዛቤ መለኪያ፡-	
CogAT (የፈተና/የግምገማ ጊዜ 12/14/26-12/17/26)	85ኛ - 89ኛ ጣምራ ውጤት በመቶኛ/Composite - 85th - 89th percentile
የአካዳሚክ ውጤት ምዘና፡-	
መዋእለ ህጻናት ፀደይ/ስፕሪንግ 2025 DIBELS (የፀደይ/የስፕሪንግ ግምገማ ጊዜ 04/05/25-06/12/25) **<u>ወይም</u>** **መዋዕለ ሕፃናት 2025 ፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት Lectura (ስፓንሽኛ ትርጉም)** (የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት 04/05/25-06/12/25)	የስፕሪንግ (ፀደይ) ወቅት 2025 DIBELS ጥንቅር ውጤት 450 ወይም ከዚያ በላይ **<u>ወይም</u>** የስፕሪንግ (ጸደይ) 2025 Lectura 438 ወይም ከዚያ በላይ
1ኛ ክፍል የትምሕርት አመት 2026 የጸደይ/የስፕሪንግ ወቅት ሂሳብ MAP Growth (የትምህርት ግምገማ ጊዜ 05/04/26-06/12/26)	የስፕሪንግ ወቅት (ጸደይ) 2026 85% በመቶ ወይም ከዚያ በላይ
የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር:	
የወላጅ ግብአት የሚሞላበት ቅጽ	የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሚላል
የአስተማሪ ዳሰሳ	ነጥቦቹ ከሶስቱ ንኡስ ምድቦች ውስጥ ቢያንስ በሁለቱ ጣራ ማሚላት አለባቸው። (ፈጠራ፣ ተነሳሽነት፣ መማር)
የሠራተኞች ድጋፍ ዳሰሳ (ካስፈለገ) በትምህርት ቤት ባለሙያ ሰራተኞች የሚሞላ	የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሚላል

4ኛው መንገድ፡ CogAT ባትሪ ውጤቶች ጥምረት እና አንድ የአካዳሚክ መለኪያ (ሊተርሲ ወይም ሂሳብ) እና አንድ የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር።	
የግንዛቤ መለኪያ፡-	
CogAT (የፈተና/የግምገማ ጊዜ 12/14/26-12/17/26)	CogAT ባትሪ ውጤቶች 85 ከመቶ ወይም ከዚያ በላይ። የቃል - የአሃዝ/የቁጥር (VQ)
የአካዳሚክ ምዘና፡-	
መዋእለ ህጻናት ፀደይ/ስፕሪንግ 2025 DIBELS (የፀደይ/ስፕሪንግ ግምገማ ወቅት 04/05/25-06/12/25) **ወይም** **መዋዕለ ሕፃናት 2025 ፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት Lectura (ስፓንሽኛ ትርጉም)** (የፀደይ/የስፕሪንግ ግምገማ ወቅት 04/05/25-06/12/25)	2025 የፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት DIBELS የተቀናጀ ውጤት 450 ወይም ከዚያ በላይ **ወይም** የጸደይ/ስፕሪንግ 2025 Lectura 438 ወይም ከዚያ በላይ
1ኛ ክፍል 2026 የጸደይ/የስፕሪንግ ወቅት ሂሳብ MAP Growth (የትምህርት ምዘና ወቅት 05/04/26-06/12/26)	2026 የጸደይ/ስፕሪንግ ወቅት 85% ወይም ከዚያ በላይ
የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር:	
የወላጅ ግብአት የሚሞላበት ቅጽ	የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሚላል
የአስተማሪ ዳሰሳ	ነጥቦቹ ከሶስቱ ንኡስ ምድቦች ውስጥ ቢያንስ በሁለቱ ጣራ ማሚላት አለባቸው። (ፈጠራ፣ ተነሳሽነት፣ መማር)
የሠራተኞች ድጋፍ ዳሰሳ (ካስፈለገ) በትምህርት ቤት ባለሙያ ሰራተኞች የሚሞላ	የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሚላል

[2026-2027 ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) ልየታ/ማጣራት በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች]

4ኛ ክፍል የትምህርት አመት (SY) 2026-2027

4ኛ ክፍል ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች (GT) ለመለየት አራት መንገዶች አሉ። ለእያንዳንዱ ዘርፍ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከዚህ በታች ተገልጸዋል። 3ኛ ክፍል የስፕሪንግ ወቅት 2026 እና 4ኛ ክፍል 2026 ፎል (በልግ) መረጃ ጥቅም ላይ ይውላል። MAP ውጤቶች በአካባቢያዊ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚጠበቁ ናቸው።

የመረጃ ምንጮች	**ጠቋሚ**
Pathway 1፡ የግንዛቤ መለኪያን ብቻ መሟላት አለበት።	
የግንዛቤ መለኪያ፡-	
CogAT **(የፈተና/የግምገማ ጊዜ** 12/7/26-12/10/26)	**ከተፈታኞች የተቀናጀ ውጤት - 90 ፐርሰንት ወይም ከዚያ በላይ**
2ኛው መንገድ፡ የግንዛቤ (ኮግኒቲቭ) እና አንድ የሊተርሲ እና አንድ የሂሳብ ምዘና ማሟላት አለበት።	
የአካዳሚክ ውጤት ምዘና፡-	
CogAT **(የፈተና/የግምገማ ጊዜ** 12/7/26-12/10/26)	**ጥምር - 85 እስከ 89 ፐርሰንት**
3ኛ ክፍል 2026 የጸደይ ወቅት ወይም 4ኛ ክፍል የመኸር ወቅት MAP Growth Reading የንባብ ምዘና **(የፀደይ ወቅት የትምህርት ምዘና ወቅት** 05/04/26-06/12/26) **(የበልግ/ፎል የፈተና ቀን** 08/31/26) **<u>ወይም</u>** **3ኛ ክፍል ስፕሪንግ 2026 MCAP የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/አርትስ** **(የፀደይ/ስፕሪንግ የትምሕርት ምዘና ወቅት** 07/04/26-05/22/26)	**የፀደይ/ስፕሪንግ** 2026 MAP 85% **ወይም ከዚያ በላይ** 2026 **የፎል ወቅት (በልግ)** MAP 85% **ወይም ከዚያ በላይ** **<u>ወይም</u>** 2026 **የስፕሪንግ ወቅት** MCAP **ውጤት** 790 **ወይም ከዚያ በላይ**
3ኛ ክፍል 2026 የጸደይ/የስፕሪንግ ወቅት ሂሳብ MAP Growth **(የፀደይ/ስፕሪንግ የግምገማ ወቅት** 12/04/26-06/05/26) **<u>ወይም</u>** **2026 ስፕሪንግ 3ኛ ክፍል** MCAP **ሒሳብ** **(የፀደይ/ስፕሪንግ የግምገማ ወቅት** 07/04/26-05/22/26)	**የፀደይ/ስፕሪንግ** 2026 MAP 85% **ወይም ከዚያ በላይ** **<u>ወይም</u>** **ስፕሪንግ** 2026 MCAP **ውጤት** 790 **ወይም ከዚያ በላይ**
3ኛው መንገድ፡ የግንዛቤ መለኪያ እና አንድ የአካዳሚክ መለኪያ (ሊተርሲ ወይም ሂሳብ) እና አንድ የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር ማሟላት አለበት።	

የግንዛቤ መለኪያ፦	
CogAT (የፈተና/የግምገማ ጊዜ 12/7/26-12/10/26)	የተቀናጀ ውጤት 85 እስከ 89 ፐርሰንት።
የአካዳሚክ ምዘና፦	
3ኛ ክፍል 2026 የጸደይ ወቅት ወይም 4ኛ ክፍል የመኸር ወቅት MAP Growth Reading የንባብ ምዘና (የፀደይ የትምህርት ምዘና ወቅት 05/04/26-06/12/26) (የበልግ/ፎል የፈተና ቀን 08/31/26) **<u>ወይም</u>** **3ኛ ክፍል ስፕሪንግ 2026 MCAP የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/አርትስ** (የፀደይ/ስፕሪንግ ግምገማ ወቅት 07/04/26-05/22/26)	የፀደይ/ስፕሪንግ 2026 MAP 85% ወይም ከዚያ በላይ የፎል ወቅት (በልግ) 2026 MAP 85% ወይም ከዚያ በላይ **<u>ወይም</u>** የፀደይ/ስፕሪንግ MCAP 2026 ውጤት 790 ወይም ከዚያ በላይ
3ኛ ክፍል የትምሕርት አመት 2026 የጸደይ/የስፕሪንግ ወቅት ሂሳብ MAP Growth (የፀደይ/ስፕሪንግ የግምገማ ወቅት 12/04/26-06/05/26) **<u>ወይም</u>** **3ኛ ክፍል 2026 ስፕሪንግ MCAP ሒሳብ** (የፀደይ/ስፕሪንግ የግምገማ ወቅት 07/04/26-05/22/26)	የፀደይ/ስፕሪንግ 2026 MAP 85% ወይም ከዚያ በላይ **<u>ወይም</u>** 2026 ስፕሪንግ MCAP ውጤት 790 ወይም ከዚያ በላይ
ዝርዝር የባህሪ ማረጋገጫ፦	
የወላጅ ግብአት ቅጽ	የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሚላል
የአስተማሪ ዳሰሳ	ነጥቦቹ ከሶስቱ ንኡስ ምድቦች ውስጥ ቢያንስ በሁለቱ ጣራ ማሚላት አለባቸው። (ፈጠራ፣ ተነሳሽነት፣ መማር)
የሠራተኞች ድጋፍ ዳሰሳ (ካስፈለገ) በትምህርት ቤት ባለሙያ ሰራተኞች የሚሞላ	የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሚላል
4ኛው መንገድ፣ CogAT ባትሪ ውጤቶች ጥምረት እና አንድ የአካዳሚክ መለኪያ (ሊተርሲ ወይም ሂሳብ) እና አንድ የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር።	
የግንዛቤ መለኪያ፦	

CogAT **(የፈተና/የግምገማ ጊዜ 12/7/26-12/10/26)**	CogAT **ባትሪ ውጤቶች 85 ከመቶ ወይም ከዚያ በላይ።** **የቃል- የቁጥር/አሃዝ**
የአካዳሚክ ምዘና፡-	
3ኛ ክፍል 2026 የጸደይ ወቅት ወይም 4ኛ ክፍል የመኸር ወቅት MAP Growth Reading የንባብ ምዘና **(የፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት ግምገማ** 12/04/26-06/05/26) **(ፎል የትምህርት ምዘና ቀን** 08/31/26) ***<u>ወይም</u>*** **3ኛ ክፍል ስፕሪንግ 2026 MCAP የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/አርትስ** **(የፀደይ/ስፕሪንግ ወቅት ግምገማ** 07/04/26-05/22/26)	**የፀደይ/ስፕሪንግ** 2026 MAP 85% **ወይም ከዚያ በላይ** **የፎል ወቅት (በልግ)** 2026 MAP 85% **ወይም ከዚያ በላይ** ***<u>ወይም</u>*** **ስፕሪንግ** 2026 MCAP **ውጤት** 790 **ወይም ከዚያ በላይ**
3ኛ ክፍል የትምሕርት አመት 2026 የጸደይ/የስፕሪንግ ወቅት ሂሳብ MAP Growth **(የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት** 12/04/26-06/05/26) ***<u>ወይም</u>*** **3ኛ ክፍል ስፕሪንግ 2026 MCAP ሒሳብ** **(የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት** 07/04/26-05/22/26)	**የፀደይ/ስፕሪንግ** 2026 MAP 85 **በመቶ (%) ወይም ከዚያ በላይ** ***<u>ወይም</u>*** **ስፕሪንግ** 2026 MCAP **ውጤት** 790 **ወይም ከዚያ በላይ**
የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር:	
የወላጅ ግብአት የሚሞላበት ቅጽ	**የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሟላል**
የአስተማሪ ዳሰሳ	**ነጥቦቹ ከሶስቱ ንኡስ ምድቦች ውስጥ ቢያንስ በሁለቱ ጣራ ማሟላት አለባቸው።** **(ፈጠራ፣ ተነሳሽነት፣ መማር)**
የሠራተኞች ድጋፍ ዳሰሳ **(ካስፈለገ) በትምህርት ቤት ባለሙያ ሰራተኞች የሚሞላ**	**የአጠቃላይ ነጥብ ጣራ ያሟላል**

7ኛ ክፍል የትምህርት አመት (SY) 2026-2027

7ኛ ክፍል ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) መለያ ሁለት መንገዶች አሉ። ለእያንዳንዱ ዘርፍ የሚያስፈልጉ መስፈርቶች ከዚህ በታች ተገልጸዋል። 6ኛ ክፍል የስፕሪንግ ወቅት 2026 እና 7ኛ ክፍል 2026 ፎል (በልግ) መረጃ ጥቅም ላይ ይውላል። MAP ውጤቶች በአካባቢያዊ እና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚጠበቁ ናቸው።

የመረጃ ምንጮች	**ጠቋሚ**
1ኛው መንገድ፡ አራት የትምህርት መለኪያዎችን ማሟላት አለበት **2ኛው መንገድ፡** 3 የአካዳሚክ መለኪያዎች እና አንድ የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር ማሟላት አለበት።	
የአካዳሚክ ውጤት ምዘና፡-	
6ኛ ክፍል 2026 የጸደይ ወቅት ወይም 7ኛ ክፍል የመኸር ወቅት MAP Growth Reading የንባብ ምዘና (የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት 12/04/26-06/05/26) (የፎል (በልግ) ግምገማ መስኮት 08/31/2026)	የፀደይ/ስፕሪንግ 2026 MAP 85 በመቶ (%) ወይም ከዚያ በላይ የፎል ወቅት (በልግ) 2026 MAP 85% በመቶ ወይም ከዚያ በላይ
6ኛ ክፍል የጸደይ ወቅት ወይም 7ኛ ክፍል የመኸር ወቅት 2026 MAP Growth Math ሂሳብ (የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት 12/04/26-06/05/26) (የፎል (በልግ) ግምገማ መስኮት 09/03/2026)	የፀደይ/ስፕሪንግ 2026 MAP 85 በመቶ (%) ወይም ከዚያ በላይ የፎል ወቅት (በልግ) 2026 MAP 85% በመቶ ወይም ከዚያ በላይ
6ኛ ክፍል ስፕሪንግ 2026 MCAP የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/አርትስ (የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት 07/04/26-05/22/26)	ስፕሪንግ 2026 MCAP ውጤት 777 ወይም ከዚያ በላይ
6ኛ ክፍል ስፕሪንግ 2026 MCAP ሒሳብ (የስፕሪንግ ወቅት (ፀደይ) ግምገማ መስኮት 07/04/26-05/22/26)	ስፕሪንግ 2026 MCAP ውጤት 775 ወይም ከዚያ በላይ
የባህሪ ማረጋገጫ ዝርዝር:	
የወላጅ ግብአት የሚሞላበት ቅጽ	ጣራውን ማሟላት አለበት
የአስተማሪ ዳሰሳዎች - እንግሊዝኛ እና ሂሳብ	ከሶስቱ ንዑስ ምድቦች ቢያንስ የሁለቱን ጣራ ያሟላል። (ፈጠራ፣ ተነሳሽነት፣ መማር)
የሰራተኞች ድጋፍ መስጫ ቅጽ (አማራጭ) በትምህርት ቤት ባለሙያ ሰራተኞች የሚሞላ	መመዘኛውን ያሟላል

2026-2027 ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) ልየታ/ማጣራት በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

ባለ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ መለያ - 2026-2027 FAQs/በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

ተማሪዎች እንደገና የሚመለመሉት በምን ሁኔታ ነው?

2026–2027 የትምህርት አመት፣ በአሁኑ ወቅት 4ኛ ወይም 7ኛ ክፍል የሚማሩ፣ በቀደሙት ዓመታት ልዩ ተሰጥኦ (gifted and talented) መለያ መስፈርቶችን ያላሟሉ፣ እና 'አማራጭ የመማር ውጤቶች'/ALOs (Alternative Learning Outcomes - ALOs) ያላገኙ ተማሪዎች እንደገና ማጣራት ይደረግላቸዋል።

የአንድ ተማሪ መረጃ በመላው የትምሕርት ስርዓቱ የተቀመጡትን 'ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች' (gifted and talented) መስፈርቶች የማያሟላ ከሆነ፣ ሌሎች አማራጭ MCPS የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ይቻላል?

በየክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች ወጥ የሆነ የትምሕርት ችሎታ ምዘና መለኪያዎችን ለማስቀጠል፣ የትምህርት ዘርፍ ሱፐርቫይዘሮች እና የዲስትሪክት ዳይሬክተሮች MCPS የትምሕርት አመት 2026–2027 የክፍል ደረጃ ምዘና የጊዜ ሠሌዳ (Grade Level Assessment Calendar) የተወሰኑ የአካዳሚክ መረጃ ምንጮችን አጽድቀዋል። አስፈላጊ የሆኑ የተማሪ የአካዳሚክ ምዘና ውጤቶች ሲጓደሉ ብቻ፣ አማራጭ የመረጃ ምንጮች ግምት ውስጥ ይገባሉ። በዚህ መሠረት፣ «Accelerated and Enriched Instruction» (የተፋጠነ እና የበለጸገ ትምህርት) ቢሮ፣ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ፣ ከአንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ከሆኑ የስቴት ደረጃ ምዘናዎች (ለምሳሌ፡- MAP፣ MCAP) የተገኙ ወቅታዊ መረጃዎችን በመጠቀም የሚከናወን ግምገማ ሊያካሂድ ይችላል።

ለተጓደሉ የወላጅ ግብዓት ቅጾች (Parent Input Forms) ግምገማዎች አይሰጡም። ለአንድ ተማሪ ከአንድ በላይ ቅጾች ከቀረቡ፣ ከፍተኛው ውጤት ጥቅም ላይ ይውላል። እባክዎ ቅጾቹ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ በኤሌክትሮኒክስ መቅረባቸውን ያረጋግጡ፤ ምክንያቱም ከጊዜ ገደቡ በኋላ የሚቀርቡ ቅጾች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

ለዚህ ሂደት MAP የሚተገበረው እንዴት ነው?

NWEA- 2025 ብሄራዊ ድንጋጌዎች እና MCPS የአካባቢ ትምህርት ውጤት መስፈርቶች ባለተሰጥኦ እና ከፍተኛ የትምህርት ችሎታ ያላቸውን የመለየት ሂደት ላይ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

በአካባቢው ተቀባይነት ያላቸው ውጤቶች (locally normed scores) ምንድን ናቸው? እና በማጣራት ሂደት ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ ይውላሉ?

የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ (MSDE) የላቀ ደረጃ መስፈርቶችን እና ተሰጥኦ እና ልዩ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የተዘጋጀውን የትምህርት ሞዴል መመሪያዎች መሠረት በማድረግ፣ MCPS ሁሉንም የተማሪ ቡድኖች—ብዝሃ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን፣ እና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት ያለባቸውን ተማሪዎች ጭምር—ያካተተ፣ ፍትሃዊ እና ልዩ ተሰጥኦቸውን እና ትምህርት የመቅሰም አቅማቸውን ለይቶ የመማር ችሎታቸውን የሚመጥን አሰራር ለመፍጠር ቁርጠኛ ነው። በአካባቢ ተቀባይነት ያላቸው መመዘኛዎችን መጠቀም፣ በብሔራዊ አማካይ ውጤቶች ላይ ብቻ ከመተማመን ይልቅ፣ ተመሳሳይ የትምህርት ተሞክሮ ባላቸው ተማሪዎች መካከል የፈተና ውጤቶችን በማነጻጸር የግምገማ ውጤቶችን መገምገም ያስችለናል። 4ኛ እና 7ኛ ክፍል ለሚሰጠው MAP ምዘና፣ በአካባቢው ተቀባይነት ያላቸው ውጤቶች የሚመሰረቱት ተመሳሳይ FARMS (የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ አገልግሎት) ተጠቃሚ ትምህርት ቤቶችን በመቧደን ነው። ይህ በጠንካራ ውጤት ላይ የተመሰረተ አካሄድ፤ እንቅፋቶችን ለማስወገድ፣ እድሎችን ለማስፋት፣ እና ለመላው የትምህርት ስርአት ማህበረሰባችን ልዩነትና ብዝሃነት እውቅና ለመስጠት ይረዳል።

ትምህርት ቤቶች በአካባቢ ትምህርት ቤት ስለሚገኝ የበለጸገ እና/ወይም የተፋጠነ የትምህርት ፕሮግራም እድሎች ውሳኔ የሚሰጡት እንዴት ነው?

የትምህርት ቤት ቡድኖች የማስተማር ውሳኔዎችን ለመስጠት የተለያዩ የተማሪ መረጃዎችን ይገመግማሉ። እነዚህ የመረጃ ነጥቦች የውጤት መግለጫዎችን፣ የክፍል ትምህርት ምዘናዎችን፣ MAP ውጤቶችን፣ የንባብ ደረጃዎችን እና የትምህርት ክፍል ምልከታዎችን ያካትታሉ። ምንም እንኳን ተሰጥኦ ያላቸው (GT) ተማሪዎች ተለይተው እንዲማሩ ቢታሰብም፣ የተጠናከረ ወይም የተፋጠነ ትምህርት ለማግኘት በመደበኛነት «ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች» (GT) መሆን አይጠበቅባቸውም። የአካባቢ ትምህርት ቤቶች፣ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት ለማሟላት ሲባል፣ በዋና ዋና የትምህርት ዘርፎች ላይ እንደሁኔታው የሚስተካከል

የቡድን/flexible grouping አደረጃጀቶችን እና ለእነሱ የተዘጋጁ የበለጸጉ ትምህርቶችን (ለምሳሌ፦ የምርምር ተግባራትን፣ ጠንካራ የትምህርት ተግባሮችን፣ እና የስነ-ጽሑፍ ጥናቶችን) ይሰጣሉ።

3ኛ እና 5ኛ ክፍል ባለተሰጥኦ እና የላቀ ችሎታ (GT) ልየታ እና በማዕከላዊ የችሎታ ምዘና መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ባለ ተሰጥኦ ከፍተኛ ችሎታ ያላቸው 'GT' ተማሪዎችን ለይቶ ማወቅ እና ማዕከላዊ ግምገማ ማድረግ ለተለያዩ ዓላማዎች ይጠቅማል። GT (ተሰጥኦ ያላቸው) ተማሪዎችን የመለየት ሂደት 2ኛ፣ 4ኛ፣ እና 7ኛ ክፍል ደረጃ ላይ የሚከናወን አጠቃላይ የተማሪዎችን ትምህርት የመቅሰም ችሎታ የማጣራት ተግባር ሲሆን፣ ዓላማውም የአካባቢ ትምህርት ቤቶች የማስተማር ዕቅዳቸውን ለማዘጋጀት የተማሪዎችን አቅምና ጥንካሬዎች ለመለየት ነው። በሌላ በኩል፣ 3ኛ እና 5ኛ ክፍል ማዕከላዊ ግምገማ (Central Review)፤ ተማሪዎችን ለልዩ ሪጅናል ፕሮግራሞች («Centers for Enriched Studies» እና «middle school magnets» ለመሳሰሉት) በሚደረግ የዕጣ አወጣጥ (lottery) ሂደት ውስጥ ለማካተት፤ የተማሪዎችን የውጤት መግለጫዎች (report cards)፣ የንባብ ደረጃዎች እና «MAP» ውጤቶችን ይገመግማል። በእነዚህ ሪጅናል ፕሮግራሞች ውስጥ ለመመደብ GT ምደባ አያስፈልግም፣ እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች የተማሪ GT ወይም የማዕከላዊ ግምገማ ውጤት ምንም ይሁን ምን ያለማቋረጥ የበለፀገ/የዳበረ ትምህርት ይሰጣሉ።

በሌላ ት/ቤት አስቀድሞ የተደረገ የባለተሰጥኦ እና የላቀ የትምህርት ችሎታ ልየታ ግንዛቤ ውስጥ ይገባል ወይ?

አዎን። MCPS ከዲስትሪክቱ ውጭ የተሰጡ GT (ባለ ተሰጥኦ ተማሪዎች) ምደባዎችን፣ ተገቢ ማስረጃ ከቀረበ ይቀበላል። ወላጆች/አሳዳጊዎች 2026-27 የቅድመ GT (ባለተሰጥኦ እና በብቃት የላቁ ተማሪዎች) መለያ ቅጽ መሙላት አለባቸው። እንዲሁም፣ የመለያ/የብቁነት ደብዳቤውን እና ይፋዊ የፈተና ሪፖርት ለትምህርት ቤታቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት GT ኃላፊ (Liaison) ወይም ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 'Accelerated and Enriched Instruction Support Teacher' (AEIST) ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤ እነዚህ ሰነዶች 'Accelerated and Enriched Instruction' (AEI) ክፍል ተልከው ይገመገማሉ።

በቡድን ወይም በተናጠል የሚሰጡ የግንዛቤ ችሎታ ምዘናዎች ግምት ውስጥ ይገባሉ?

አዎን። አንድ ተማሪ MSDE (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ) የተፈቀደ፣ በቡድን ወይም በተናጠል የሚሰጥ የአዕምሮ ብቃት (cognitive ability) ምዘና ውጤት ማስረጃ ካለው/ካላት፣ ወላጅ/አሳዳጊ "ባለ ተሰጥኦ እና ከፍተኛ ችሎታ/ብቃት ላላቸው ተማሪዎች የሚሰጥ እውቅና ለማግኘት 2026-2027 የወላጅ/አሳዳጊ መጠየቂያ ቅጽ መሙላት አለባቸው። እንዲሁም፣ አስፈላጊውን ማስረጃ ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "ለተሰጥኦ እና ከፍተኛ የትምህርት ብቃት ያላቸው ተማሪዎች ፕሮግራም (GT) አስተባባሪ" ወይም ለመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት "ለተፋጠነ እና የበለጸገ ትምህርት ድጋፍ ሰጪ መምህር (AEIST)" ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ፈቃድ ባለው የውጭ የስነ-ልቦና ባለሙያ የሚተገበር የግለሰብ የግንዛቤ ችሎታ (ኮግኒቲቭ) ግምገማ ካቀረቡ፣ የትምህርት ቤቱ የስነ-ልቦና ባለሙያ (ሳይኮሎጅስት) እና IEP/EMT የብዝሃ ዘርፍ ቡድን ለመጨረሻ ግምገማ ወደ AEI ክፍል በኤሌክትሮኒክስ ከማቅረባቸው በፊት የማስተማሪያ ፕሮግራሞችን ለማሳወቅ እና AEI ተቀባይነት ያለው መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሪከርዶቹን ይገመግማሉ።

መስፈርቶቹ ካልተሟሉ፣ ተማሪው(ዋ) በትምህርት እቅድ ዝግጅት ላይ ግብዓት ለመስጠት በሚያገለግለው፣ አጠቃላይ MCPS የትምህርት ስርዓት በሚካሄደው የማጣራት ሂደት (2ኛ፣ 4ኛ፣ ወይም 7ኛ ክፍል) መሳተፍ ይችላል/ትችላለች።

MSDE ያፀደቀው በቡድን የሚካሄዱ የግንዛቤ ችሎታ ምዘናዎች፦

- የግንዛቤ ችሎታ ምዘና (CogAT) = Cognitive Abilities Test (CogAT)
- የናግሊሪ የአጠቃላይ ችሎታዎች ፈተና (NGAT) = Naglieri General Abilities Test (NGAT)
- ናግሊየሪ በቃል የማይደረግ ግምገማ (NNAT) = Naglieri Nonverbal Assessment (NNAT)
- የኦቲስ-ሌናን የትምህርት ቤት ችሎታ ግምገማ (OLSAT) = Otis-Lennon School Ability Assessment (OLSAT)
- የግንዛቤ ችሎታዎች ምልከታ Terra Nova InView of Cognitive Skills

MSDE **የፀደቁ የተናጠል የአእምሮ እውቀትና የግንዛቤ ችሎታ ምዘናዎች፡-**

- **የግንዛቤ ችሎታ ምዘና ስርዓት** (CAS2) **የማጣሪያ ቅጾች**
- **ለልጆች የኩፍማን የተጣመሩ ግምገማዎች/ምዘናዎች=**Kaufman Assessment Battery for Children (KABC-II/KABC-III)
- **ስታንፎርድ/በይነት ኢንተለጀንስ መለኪያ =** Stanford/Binet Intelligence Scales
- **ዌችስለር የልጆች ችሎታ መመዘኛ =** Wechsler Intelligence Scale for Children (WISC)
- Wechsler Nonverbal Scale of Ability (WNV)
- **የዌቸስለር ቅድመ ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የግንዛቤ ችሎታ መለኪያ** (WPPSI) **=** Wechsler Preschool Primary Scale of Intelligence (WPPSI)
- **የግንዛቤ ችሎታ ፈተና** Woodcock-Johnson Test of Cognitive Ability